መደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብዕ

የአማርኛ ቋንቋ እና ሥነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል


# የድህረ ምረቃ መረሃ-ግብር

## በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂልን ሲማሩ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፈተሽ (በ7ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


በ

ውብእጅግ ታከለ



መስከረም/2014 ዓ.ም

ባሌ ሮቤ

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂልን ሲማሩ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፈተሸ (በ7ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


መደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብዕ

የአማርኛ ቋንቋ እና ሥነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መረሃ-ግብር

በ


ውብእጅግ ታከለ

የመታወቂያ ቁጥር PGAE/011/12

የጥናቱ አማካሪ

ግርማ ኃይሉ ዶ/ር


ተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት

የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ


መስከረም/2014 ዓ.ም

ባሌ -ሮቤ

**መደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ**

**የማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብዕ**

**የአማርኛ ቋንቋ እና ሥነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል**

## የድህረ ምረቃ መረሃ-ግብር

አፋቸውን በኦሮሚኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ንግግርን ሲማሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መፈተሸ (በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በጎባ ወረዳ በወ-ልተኢ ጢሎ እና በሲንጃ ፣፤ ነኛ ደረጃ ት/ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ በተግባራዊ ስነ- ልሳን አማርኛን ማስተማር ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያ በውብእጅግ ታከለ የቀረበ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን ጥራትና መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈታኝ ቦርድ አባላት

አማካሪ ______________________________ፊርማ_____________ቀን____________

የውጭ ፈታኝ__________________________ ፊርም____________ ቀን __________

የውስጥ ፈታኝ__________________________ ፊርማ___________ ቀን____________

**ማረጋገጫ**

ይህ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግርን ሲማሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መፈተሽ በሚል ርዕስ በመደ ወላቡ ዩኒቨርስቲ በማህበራቂ ሳይንስና ስነ-ሰብዕ ኮሌጅ ለአርትስ ማስትርስ ዲግሪ ያቀረብኩት የጥናት ጽሁፍ የራሴ መሆኑን እና በጥናቱ የተጠቀምኩባቸው መረጃ ጽሁፎች በትክክል ዋቢዎች የሆኑና መደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡

ስም________________________________

ቀን__________________________

ፊርማ_________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ለዚህ ደረጃ ላበቃኝ አምላክ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠልም ጥናቱ ተጀምሮ እስኪያበቃ ድረስ የጥናቱን ረቂቅ ደጋግሞ በማንበብ ማስተካከያ እና ምክር በመለገስ ውድ ጊዜያውን መስዋት በማድረግ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ መምህሬ እና አማካሪዬ ለዶ/ር ግርማ ሀይሉ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠልም በጥናቱ ረቂቅ ላይ ምክሮችን እና አስተያየቶችን በመስጠት ላበረታቱኝ መምህሬ ለዶ/ር ፍቅሩ ወ/ኪዳን አክብሮት እና ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም ለዚህ ደረጃ እንድደርስ ለረዱኝ መምህሬ ለዶ/ር መሀመድ ጀማል ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በመቀጠልም ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አስፈላጊውን መረጃ እና ማብራሪያ ለሰጡኝ ውድ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን እና ተመሪዎች ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እንዲሁም ይህንን ትምህርት እንድማር ላበረታታኝ እና በዚህ የትምህርት ጊዜ የቤተሰብ ማስተዳደር ሀላፊነቱን ወስዶ ከፍተኛ እርዳታ ላደረገልኝ ውድ ባለቤቴ መምህር ደረጀ ስዩም ከልብ የመነጨ ምስጋና ይድረስልኝ፡፡

# ይዘት ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና ........ i
ይዘት ማውጫ ........ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ v
የአባሪዎች ማውጫ ........ vi
አጠቃሎ ........ vii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር ........ 4
1.3.የጥናቱ አላማ ........ 6
1.3.1.የጥናቱ ዋና አላማ ........ 6
1.3.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 6
1.4. የጥናቱ ዓብይት ጥያቄቆች ........ 6
1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 7
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 7
1.7 የጥናቱ አወቃቀር ........ 8
ምዕራፍ ሁለት ........ 9
ክለሳ ድርሳናት ........ 9
2.1. ንግግር ምንድ ነው? ........ 9
2.2. የንግግር አስፈለሰጊነት ........ 10
2.3. የንግግር ትምህርት አስፈላጊነት ........ 11

2.4. በክፍል ውስጥ የንግግር ኪሂል ትምህርት ወቅት የመምህሩ ስራና ሀላፊነት...... 13

2.5. የስህተት ምንነት...................................................................... 13

2.6. የንግግር ስህተት ትንተና.......................................................... 16

2.7. የንግግር ክሂል ሲማሩ የተማሪዎች ድርሻ.......................................... 18

2.8. የንግግር ኪሂልን ትምህርትን አዳጋች የሚያደርጉ ነገሮች ......................... 18

2.8.1.የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ..................................................... 19

2.8.2. የውስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ.......................................................... 19

2.8.3. ስነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች ....................................................... 20

2.8.4.ሰዋሰዋዊ ችግር ................................................................... 21

2.9 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት.............................................................. 22

ምዕራፍ ሦስት ........................................................................... 24

የጥናቱ ዘዴ ................................................................................. 24

3.1. የጥናቱ ስልት ........................................................................ 24

3.2. ተጠኚዎች .............................................................................. 24

3.2.1 የጥናቱ አካባቢ........................................................................ 24

3.2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች.................................................................. 25

3.2.3. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ.............................................. 25

3.2.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ...................................................... 25

3.2.5. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ .................................................. 26

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ......................................................... 27

3.3.1 የመማሪያ ክፍል ውስጥ የትምህርት አተገባበር ምልከታ ...................... 27

3.3.2 የጽሁፍ መጠየቅ........................................................................ 28

3.3.3. ቃለ መጠይቅ ......................................................................... 29

3.3.4. ፈተና...................................................................................... 29

3.4.የጥናቱ ስነ- ምግባራዊነት ............................................................ 30

3.5.የትናቱ አስተማማኝነት ................................................................. 31

3.6. የመረጃ አደረጃጀት እና አተናተን ዘዴ ............................................ 31

ምዕራፍ አራት ............................................................................ 33

4. የመረጃ ትንተና ውጤት.................................................................. 33

4.1 የመረጃ ትንተና.......................................................................... 33

4.1.1. አፋቸውን በኦሮሚኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንምን ናቸው? ................................ 33

4.1.2. አማርኛ ኢ- አፈ ፈት ተማሪዎች በአማርኛቋንቋ ነግግር ሲያደርጉ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጮቻቸው ምን ሊሆኑ የችላሉ ?................ 48

4.1.3. በመማር ማስተማር ሂደት ፣ በንግግር ላይ የሚታዩ ስህተቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የመፍትሔ ሀሳቦች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? ............ 50

4.2. የውጤት ማብራሪያ................................................................. 57

ምዕራፍ አምስት.......................................................................... 59

ማጠቃለያና አስተያየት.................................................................. 59

5.1.ማጠቃለያ ............................................................................. 59

5.2. አስተያየት............................................................................ 60

ዋቢ መጻህፍት.............................................................................. 62

አባሪዎች.................................................................................. 67

## የሠንጠረዥ ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ሠንጠረዥ አንድ፡- በሁለት አራሚዎች የተሰጠ ፈተና አማካኝ

ውጤት ትንተና........................................................................................36

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የክፍል ውስጥ ምልከት የመከታተያ ቅጽ(ቸክ ሊስት)..........47

ሠንጠረዥ ሶስት ፡- ቃለመጠይቃ የተደረገላቸው መምህራን ዳራዊ መረጃ.............52

## የአባሪዎች ማውጫ

**አባሪ፡-ሀ** የንግግር የቃል ፈተና ጥያቄዎች.......69

**አባሪ፡-ለ** የቃል ፈተና ጥያቄዋች እና መልሶቻቸው.......70

**አባሪ፡- ሐ** አራሚ በንግግር ንዑሳን ክሂሎች ላይ በመማስረት ለጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የተሰጡ ውጤት.......74

**አባሪ፡-መ** አራሚ 2 በንግግር ንዑሳን ልሂሎች ላይ በመመስረት ለጥናቱ ተተኳሪነት ተማሪዎች የተሰጠ ውጤት.......77

**አባሪ፡-ሠ** የክፍል ውስጥ የመከታተያ ቅጽ (cheek list).......80

**አባሪ፡-ረ** የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት የሚያዝበት ቅጽ.......81

**አባሪ፡-ሰ** የመወያያ ጥያቄዎች እና የውይይቱ ምላሾች.......82

**አባሪ፡-ሸ** የተማሪዎች ስም አጠቃቀም ዳራዊ መረጃ መመዝገቢያ ቅጽ.......85

**አባሪ፡- ቀ** ክፍል አንድ፡- የመምህራን ዳራዊ መረጃ.......86

**አባሪ፡-በ** ክፍል ሁለት፡- መምህራን የቀረቡ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች.......87

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግርን ሲማሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መፈተሸ በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሩነት ላይ በማድረግ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ የገላጭ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይህን አላማ ለማሳካት የወል-ተኢ ጢሎ እና የሲንጃ ፲ኛ ደረጃ ት/ቤት በአመቺ ንሞና ሊመረጥ ችሏል፡፡ ከትምህርት ቤት ውስጥ 48 ኢ- አፈ ፈት ተማሪዎች በጥናቴ ተተኳሪነት ተወስደዋል፡፡ ለተጠኚ ተማሩዎችም ፈተና ፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና የቡድን ተኮር ውይይት በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም አማርኛ ቋንቋን 7ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መመ ህራን በጥቅል ንሞና በመውሰድ ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ የጥናቴ መረጃዎችን በመጠናዊና አይነታዊ የመረጃ ትንተና ስልቶች ተብራርተዋል፡፡ በአጠቃለይ በጥቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች አግባብነት ባለው መንገድ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡ በመጨረሻም በኢ- አፈ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ወቅት ያለባቸው ችግር ምን እንደሆነ በመግለጽ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ በችንዲሁም በጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው ውጠየት እንደሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋን በኢ- አፈ ፍት ተማሪዎች ዘንድ ማጎልበት የሚቻለው የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያግዙ እና ሊያጠናክሩ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ ጠቃሚ አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

ለበርካታ ዘመናት የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ለንግግረ ክሂል ትኩረት የነፈገ ነበር (bailey 2006 ፣ 120)፡፡ በሂደት ግን አዳምጦ የመናገር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ለትምህርት በሚቀርበው ቋንቋ የመግባባት ብቃታቸው ከፍ እንዲል የማድረግ ዓላማ ነበር ፤ ዳሩ ግን ሽምደዳ ተኮር የሆነ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የሚናገሩትን ቃላት ፍቺ የማያውቁ ተማሪዎች ከመፍጠር በዘለለ የተማሪዎችን የንግግር ክህሎት ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ እንዳልቻለ Dinzil (1987) እና Bailey (2006) አመልክተዋል፡፡ እንዲያውም አቀራረቡም ቸተማሪዎችን የሚያዳክም እና የሚያሰለች ከመሆኑ የተነሳ ተማሪዎቹ በሚማሩት ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ የሆነ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርጓል ይላሉ፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን ማዳበርና ሀሳባቸውን በንግግር መግለጽ ይችሉ ዘንድ በቋንቋ የርስ በርስ መስተጋብር ማሳደግ አለባቸው የሚለው እሳቤ ግንዛቤ ማግኘት ችሏል፡፡ በአንጻሩ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ግዜ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል በአግባቡ ካልተስተናገደ በስተቀር በተፈለገው ደረጃ ውጤታማ መሆን እንደማይችል መገንዘብ አያዳግትም፡፡

ቋንቋ በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ አስፈላጊ እና ጠቃሚ የሆነ ስረእተ ያለው ዲምጻዊ የመግብቢያ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ ቋንቋን መጠቀም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የእርስ በርስ መስተጋብር እየፈጠረበት መምጣቱና አሁንም እየተገለገለበት ያለ መሳሪያ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ የሰው ልጅ ህልውና ከቋንቋ ውጪ ማሰብ ከቶውንም የሚቻል አይሆንም፡፡

ቋንቋን ስናስብ በአመዛኙ መግባቢያ ስለሆነው ንግግር እናነሳለን፡፡ ስለዚህም ማንኛውም ጤናማ አንደበት ያለው ሰባዊ ፍጡር ከመሰሎቹ ጋር ለሚኖረው መስተጋብር ንግግር የጎላ ስፈራ የሚሰጠው ነው፡፡ በባህሩ ዘርጋው (2006)

ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት መሰረት አንድ ሰው ቋንቋን አወቀ የሚባለው ቋንቋውን መናገር ሲችልና በቋንቋው ሀሳቡን መግለጽ ሲችል ነው፡፡

ሰዎች ቋንቋን በመጠቀም ሀሳባቸውን ለሌሎች ሰዎች መጋራትና የሌሎችንም ሀሳብ እንደዚሁ በቋንቋ አማካንነት መቀበል ይችላሉ፡፡ Cross (1991 ፤ 121) ንግግርን አስመልክተው እንደገለጹት "ከአራት የቋንቋ ክሂል ዘርፎች መካከል ንግግር ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ ስለዚህም ክሂሉ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል" በማለት ያስገነዝባሉ፡፡ ይህ ማለት ግን ሌሎቹ የቋንቋ ህሂሎች ትኩረት አያሻቸውም ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም በተግባር ሲታይ ሁሉም ክሂሎች የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

Bygate (1987) ቋንቋ ለአንድ ግለሰብ ወይም ዘር ብቻ በተናጠል ተለይቶ ያልተሰጠ ፤ በይዘቱ ድንበር የለሽ አለም አቀፋዊ የሆነ እርስ በርስ ለመግባቢያነት የሚገለገሉበት ወይም የሚለዋወጡበት ስረአት ያለው የድምጾች እና የቃላት ቅንብር ያገላለጽ ሥርአት ነው፡፡ ለምሳሌ በአገራችን ተጨባጭ ሁታ እንኳን ሲታይ አንድ ሰው ከአንድ ቋንቋ በላይ ሲናገር መመልከታ የተለመደ ነው፡፡

ቋንቋ በጥቅሉ ሥነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ጥምር አገልግሎቶች ያሉት መሆኑን በድሉ ዋቅጅራ (1996) ይጠቁማሉ፡፡ ሰውን ከእንሰሳት ከለዩት ክስተቶች አንዱና ዋነኛው መንገድ ንግግር ሲሆን ፤ ለረጅም ዘመናትም ከሰው ልጅ ጋር አብሮ ኖሯል፡፡

የሰው ልጅ በእለት ከእለት ንሮው በሚያደርገው ተራክቦና በሚፈጽመው ድጊት በንግግር እርስ በርሱ መግብብቱ ወይም ሀሳብ ለሀሳብ መለዋወጥ ይችላል፡፡ ቋንቋ መናገር ስረአት ባለው መንገድ መከወን ያለበት ነገር ነው፡፡ ይህም ማለት ቋንቋን መናገር ማለት ደግሞ አንድ ሰው በሚያወቀውና በሚናገረው ቋንቋ ሀሳቡን ስረአት ባለው መንገድ ለሉላው አካል ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

ንግግር በመልክት ማስተላለፊያነት የሚታወቅ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም የሰው ልጆች የአነጋገር ስልቶቻቸውን ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ስረአቶችን ባገናዘበ መልኩ ንግግር ያደርጋሉ፡፡ ሰዎች በተለያዩ መስኮች ፣ ግንኙነት ፣ ሁኔታዎች እና ስሜትቶች ውስጥ ሆነው ንግግር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በትምህርት መስክ ፣ በግብይት ፣ ወዘተ. ከሌሎች ጋር መስተጋብር ለመፍጠር ወይም የተለያዩ ስሜቶችን ለሌሎች ለማጋራት ሊሆን ይችላል፡፡

የሰው ልጅ በአፍ መፍቻ ቋንቋው ሀሳቡን ለሌሎች ቢጤዎች ውስጥ በንግግር ማጋራት ይችላል፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን ማወቅ ከቻለም እንደዚሁ ማድረግ ይችላል፡፡ ማንኛውም ጤናማ አንደበት ያለው ሰብአዊ ፍጡር ከመሰሎቹ ጋር ለሚኖረው መስተጋብር ለንግግር የሚሰጠው ቦታ ለፍተኛ ነው፡፡

በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የትምህርት ነዐላማዎች ውስጥ የንግግር ክሂልን ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በተጨማሪ ሌላ ቋንቋን በትምህርት ወይም በልምምድ ሊዳብር ይችላል፡፡ የተማሩዎችን የተግባቦት ችሎታ ማዳበር ዓይነተኛ ጠቀሜታው ተማሪዎችን በቋንቋው መግባባት እንዲችሉ መድረግ ነው፡፡ ስለዚህም በአፍ ከፍቻ ቋንቋ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ማዳበር አስፈላጊ እና ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያደርጓቸው የንግግር ተግባራት የንግግር ችሎታቸውን ማዳበር ይችሉ ዘንድ በመምህራን ሊታገዙ ይገባል፡፡ ይህን እንጂ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን ለማዳበር በሚያደርጉት ጥረት በርካታ ስህተቶችና በተለያዩ የስህተት ምንጮች ምክንያት ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ለምሳሌ፡- ሳልስና ሳድስ ፊደላትን ለይቶ መናገር መቻላቸውን፣ የሀሳብ ቅደም ተከተል ጠብቆ መናገራቸውን፣ ተገቢ ቃላት አጠቃቀም ችሎታ /ብቃት/ ያላቸው መሆኑን፣ ነጠላና ብዙ ቁጥርን ከማሰሪያ አንቀጽ ጋር አጣጥሞ መናገራቸውን የፆታ እና የመደብ ትክክለኛ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ታመሪዎች በክፍክ ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች መንነት እና ምንጮቹ ምን እንደሆኑ በጥናቱ ተዳሷል፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

Block (1997 ፣ 21) “አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የከፍተኛ ሁተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ ነው፡፡ በራስ አለመተማመንና መልእክቱን በምክንያት እና ውጤት አቀናጅቶ አለማቅረብ እንዲሂም የቋንቋውን ስረአት ጠብቆ አለመናገር ከሚታዩ ቸግሮዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው” ይላሉ፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ በየደረጃው ከሚጠበቀው የባህሪ ገጽታ ብቃት (ለውጥ) እነጻር ተማሪዎች በየትምህርታቸው ሂደት የማዳመጥ ፣ የመናገር ፣ የማንበብ እና የመጻፍ ክሂሎቻቸውን ፣እንዲሁም የስነልሳንና የስነጽፍ እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡ ከነዚህ የቋንቋ አላማወች ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማሳደግ ነው፡፡ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ በክፍል ደረጃ ተገቢነት ያላቸውን መናገር ክሂል ተግብራትን በማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስረአት በመጠቀም ሀሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ በክፍል ውስጥ መለማመድ ይኖርባአዋል፡፡ ይህም የክፍል ውስጥ በንግግር ልምምድ ውጤታማ ለማድረግ እና የንግግር ችሎታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የተለያዩ የንግግር የመለማመጃ ተግባራትን መምህራን ማከናወን ይገባቸዋል፡፡

ይህም ተግባር ከግብ ለማድረስ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚደረገው ተግብቦታዊ ሂደት ብዙ ከመናገር በመቆጠብ ቀስቃሽ እና አጋዥ መሆን ይኖርብቸዋል እንጂ አዘውትረው ከተማሪዎቹ ጋር መስተጋብር ማዱረግ አይጠበቅባቸውም፡፡ ተማሪዎችም የመናገር ክሂል ችሎታቸውን የማሻሻል ፣ የማሳደግ አላፊነት እንዲኖርባቸው ለማድረግ በጥንድ(በቡድን) በመሆን የእርስ በእርስ መስተጋብር በማድረግ የንግግር ክሂላቸውን ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል፡፡

በወልተኢ ጢሎ እና በሲንጃ ፲ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ ሲማሩ የተለያዩ ስህተቶችን ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ፡፡ አጥኚዋም ለትምህርት ቤቱ በመምህረነት ስታገለግል የኖረች መሆኑ ችግሩን በቅርበት ለማስተዋል አጋጣሚውን ፈጥሮላታል፡፡ ሆኖም ይህ ብቻውን በጥናት እስካልተረጋገጠ ድረስ የተአማኒነት ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው፡፡

በመሆኑም በወልተኢ ጢሎ እና በሲንጃ ፲ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ ሀሳባቸውን ባግባቡ አለመግለጽ

ችግር ይታያል፡፡ አንድ አንድ ለመናገር የሚደፍሩ ተማሪዎች ሊኖሩ ቢችሉ እንኳን የቋንቋውን ህግና ስረአት ያልተከተሉ በርካታ ስህተቶችን ይፈጽማሉ፡፡

ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ መማራቸው በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ስለሆነ የሚታዩ ስህተቶች በአግባቡ ካልታረሙ በስተቀር ተማሪዎች በክሂሉ ዘርፈ ብዙ ስህተቶችን ሊፈጽሙ ስለሚችሉ የንግግር ክሂላቸውን በተፈለገው መንገድ ላይዳብር ይችላል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን ክፍል ውስጥ በንግግር ሲጠቀሙ በተለያየ ምክንያቶች ስህተት ሊፈጽሙ መቻላቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ የስህተቶች ምንነትና ምንጮች የተለያዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ቁምነገሩ ይህንኑ አውቆ ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲማሩ ጥረት ማድረጉ ላይ መሆኑን (Litle wood , 1984) ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን በአግባቡ ማዳበር የሚኖርባቸው ከሆነ ክሂሉን ለማጎልበት ችሎታዊ ተጽኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን መለየት እና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥናት የማድረግ አስፈላጊነት ቸል የማይባል ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ በመረጃ ላይ ተደገፈ ግንዛቤ መኖር ይችል ዘንድ ብሎም ችግሩን ለማቃለል በጉዳዩ ላይ ስይንሳዊ መንገድን የተከተለ ጥናት የማድረግ አስፈላጊነት የግድ ይላል፡፡ ጥናት ለማድረግ የታሰበውም ከዚህ መነሻ ነው፡፡ በመሆኑም የታሰበው ጥናት የሚያተኩረው አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ምንነትና የስህተቶኡን ምንጮች በመማሩያ ክፍል ውስጥ ችግሩን መመርመር እና ለችግሩ የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ለጥናቱ መነሻ ሊሆን ችሏል፡፡

## 1.3.የጥናቱ አላማ

### 1.3.1.የጥናቱ ዋና አላማ

የጥናቱ ዋና አላማ በባሌ ዞን በጎባ ወረዳ በወልተኢ ጢሎ እና በሲንጃ አንዳኛ ደረጃ ት/ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ኪሒልን ሲማሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መፈተሽ፡፡ ሲሆን ዝርዝር አላማው ደግሞ

### 1.3.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉትዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡ እነሱም ፡-

1. አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲደርጉ በአባዛኛው የሚፈጽሙትን ስህተት መለየት፣
2. አማርኛ ኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ ለሚፈጽሙት ስህተት ምንጩ ምን እንደሆነ ለይቶ ማሳየትና
3. በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በንግግር ሂደት ላይ ለሚታዩ ስህተት እና የስህተት ምንጮች የመፍትሔ ሀሳብን መጠቆም ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓብይት ጥያቄዎች

ከዚህ ጥናት በኋላ የሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ያገኛሉ፡፡ ጥቂቶቹም፡-

1. አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው፡፡
2. አማርኛ ኢ- አፈ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጮቻቸው ምን ሊሆኑ ይችላሉ? እና
3. በመማር መስተማር ሂደት ፣ በንግግር ላይ የሚታይ ስህተቶችን ለመቀነስ የሚያስቸሉ የመፍትሔ ሃሳብንም ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉት? ናቸው፡፡

## 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ማዳበር ከሚኖረው አስፈላጊነት አኳያ በትናቱ አማካኝነት ለሚደርስበት ግኝት ለትምህርት ባለሞያዎች ሀሳብ በመጠቆም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊኖረው ይችላል፡፡

1. ጥናቱ በሚላሄድበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ መምህራን አማርኛ ኢ-አፈ ፈት የሆኑ ተማሪዎችን የንግግር ክሂል በሚያስተምሩበት ወቅት ስህተቶች አስቀድሞ በማወቅ እና በመለየት ትምህርቱ የተቃና እንዲሆን የበኩሉን እገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. በንግግር ክሂል ወቅት በኢ- አፈ ፈት ተማሪዎች ለሚታዩ ችግሮች በመማር መስተማር ሂደት ለሚሳተፉ መምህራን የመፍትሄ ሀሳባ ይጠቁማል፡፡

3. የቋንቋ ማስተማሪያ ስነ- ዘዴን ለሚቀርፁ ምሁራን በንግግር ወቅት የሚከሰቱ ችግሮች ሊቃለሉ የሚችሉበትን ሃሳብ በመጠቆም እንደ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡

4. በርዕሱ ዙሪያ ስፋትና ጥልቀት ያለው ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኝዎች (ተመራማሪዎች) ግበዓት ይሆናል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በጎባ ወረዳ ውስት ከሚገኙ ሃያ ዘጠኝ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ሁለት በጎባ ወረዳ በወልተኢ ጢሎ እና በሲንጃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው፡፡

ጥናቱ የሚያተኩረው ኢ-አፈ ፈት የሆኑ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተቶቹን ምንጮች የሚመረምር ነው፡፡ በመሆኑም የስህተት ምንጮችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብን ይጠቁማሉ፡፡ ትኩረቱም በንግግር ክሂል ላይ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች የቋንቋ ክሂል ዓይነቶችን ፣ በወረዳው የሚገኙ ሌሎች ትምህርት ቤቶችንና የክፍል ደረጃዎችን አይመለከትም፡፡

## 1.7 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናት በውስጡ አምስት ምዕራፎች አሉት ፡፡ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ስር የተካተቱ ትኩረቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ምዕራፍ አንድ፡-** መግቢያውን ክፍል የያዘ ሲሆን ፣ በውስጡም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ መነሻ ችግር፣ የጥናቱ ዋና አላማ እና ዝርዝር አላማዎች፣ የጥናቱ አበይት ጥያቄዎች ፣የጥናቱ ጠቀሜታ እና የጥናቱ ወሰን የተካተቱበት ክፍል ነው፡፡

**ምዕራፍ ሁለት፡-** የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝትን የያዘ ነው፡፡ በስሩም የንግግር ምንነት እና አስፈላጊነት ፣ የስህተት ምንነትና ትንተና ፣የንግግር ክሂል ትምህርትን ቸዳጋች የሚያደርጉ ነገሮች እንዲሁም የቀደምት ጥናዎች ቅኝት የሚሉትነ በውስጡ ያቀፈ ነው፡፡

**ምዕራፍ ሦስት፡-** የጥናቱን ዘዴ የያዘ ክፍል ነው፡፡ በስሩም የጥናቱ ስልት፣ ተጠኝዎች (በተጠኝዎች ስርም ፡- የጥናቱ አክባቢ ፣ የትምህርት ቤት አመራረጥ እና የተማሪዎች አመራረጥ) የሚሉት ሲካተቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም በዙሁ ምዕራፍ ስር ይገኛሉ እነሱም፡- ፍተና ፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ ፣ ቡድን ተኮር ውይይት እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ በመጨረሻም የመረጃ አሰባሰብ ሂደቶች ፣ የቅድመ ጥናት ፍተሸ እና የመረጃ አተናተን ስልት የቀረበበት ነው፡፡

**ምዕራፍ አራት፡-** ከፈተና እና ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ ውጤቶች በመጠናዊ የመረጃ አተናተን ስልት ያቀረቡ ሲሆኑ ከቡድን ተኮር ውይይት እና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች ደግሞ በአይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልት ተተንትነው የሚገኙበት ክፍል ነው፡፡

**ምዕራፍ አምስት፡-** በጥናቱ የታዩና ተሰጡ ገለጻዎች ዋና ዋና ነጥቦች ተጠቅሰው የተጠቃለሉበት እና የመፍትሄ ሀሳብ ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻም ዋቢ መጽሃፍት እና የተለያዩ አባሪዎች ተጠቅሰው የተቀመጡበት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1. ንግግር ምንድ ነው?

ቋንቋ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ የሰው ለረጅ ስረእት ያለው ድምጻዊ የመግብቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የሰው ልጅ በቋንቋ አማካኝነት ሀሳቡን በመግለጽ መልሶም የሚቀበልበት የእርስ በርስ መስተጋብር የሚያደርግበት እና እየተገለገለበት ያለ መሆኑን እውን ነው፡፡

Cross (1991) ንግግርን አስመልክተው እንደገለጹት ከአራቱ ክሂል ዘርፎች መካከል ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ነ አንድ ሰው እንድን ቋንቋ ያውቃል የሚባለው ቋንቋውን መናገር ሲችል ነው፡፡ ያህ ደግሞ ሁሉም ክሂሎች በንግግር ጥላ ስር የሚታቀፉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ንግግር ሰው ስሜቱን ፣ፍላጎቱን ፣ እቅዱን የሚገልጽበትና ከሌላ ሰው ጋር የሚግባባት መሳሪያ ነው፡፡ እንደዘመናዊ ስነ ልሳን ተመራማሪዎች አገላለጽ ንግግር ሰውና ሰው የሚገናኝበት አብይ የመገናኛ መሳሪያ ነው፡፡

ንግግር ህብረተሰቡ በይሁንታ የሚግባባበት ለማንኛውም ቋንቋ መሰረት የሆነ ኪሂል ሲሆን የትኛውም ማህብረሰብ ለመግባባት በንግግር ኪሂል ውስጥ ማለፍ ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም (መሰሉ 194፡36) የማንኛውም ቋንቋ መሰረቱ ድምጽ ነው፡፡ አንድ ሰው በቋንቋ ሀሳቡን የሚያስተላልፈው የተለያዩ ድምጾችን በቅደም ተከተል በመስማት ነው፡፡ (ባዬ 1987፡13) ስለዚህም አንድ ቋንቋውን የሚማር ተማሪ ስለሚማረው ቋንቋ ድምጾች በቂ የሆነ እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ እንደ አንድ የንግግር ንዑስ ኪሂል ይማረዋል፡፡

Venkabeswam, S. (1997) ንግግር ሰው ሀሳቡን ፣ አስተያየቱን ፣ ፍላጎቱን ለመግለጽ እና ማህበራዊ ትስስሮችና መወዳጀታን ለመፍጠር እንደ መሳሪያ ያገለግላል፡፡ ንግግር ስሜት ያቀፈውን ፣ አይን የተመለከተውን ወይም ከንባብና ከማዳመጥ የተቀሰመውን እውቀት መነሻ በማድረግ ሀሳብን ስረአት ባለው መንገድ ለሌላ ወገን ለማስደመጥ መሞከር ነው፡፡

ንግግር ሂደታዊ የሆነ የረጅም ጊዜ ልምምድን እንጂ ቅጽበታዊ የሆነ ልምምድን የሚከተል አይደለም፡፡ በረጅም ጊዜ ልምምድ ውስጥ ከአእምሮ ፈልቆ የሚወጣ የማሰብ ሂደቱን አወንታዊ በሆኑ ልምምድ አማካኝነት እውቀትና ሂደታዊነትን በማቀናጀት በድግግሞሻዊ ልምምድ የሚዳብር መሆኑን የገለጹት krou (1997 ) Byme(1988)ናቸው፡፡

ስለዚህ የንግግር ኪሂል ማለት ማንኛውም ማህበረሰብ ከሰው ጋር ወይም ከማንኛውም ግለሰብ ጋር ለመግባባት የንግግር ኪሂልን መጠቀም የግድ ይለዋል፡ ሸዋዬ (1981፡1)29-60) ንግግርን ሲገልጹ ሀሳቦችን ለመግለጽ የምንገለገላቸው ዘዴዎች በንግግር የምንገለገልበት ድርሻ ከሌሎች ኪሂሎች ጋር ሲነፃር ከፍተኛ ድርሻ ይይዛል፡፡ በመሆኑም ስለ ንግግር ኪሂል ምንነት በተለያዩ ምሁራን እንደተገለጸው፣ ንግግር ማንኛውም ሰው ለመግባባትና ሀሳቡን ለመግለጽ ያስችለው ዘንድ የቋንቋውን ስርአትና ህግጋት ጠብቆ መልዕክቱ በሰመረና በተዋጣለት መንገድ እንዲተላለፍ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

## 2.2. የንግግር አስፈለሰጊኑት

የሰው ልጅ የአፈ መፍቻ ቋንቋውን በመጠቀም በንግግር ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር የእለት እንቅስቃሴውን ሲተገብር መኖሩ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ንግግር ከራቱ ክሂሎች በማመንጫ ወይም በመልክት መስተለሰለፊያነት የሚታወቅ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም ከሚደረግባቸው ምክንያዎች ውስጥ ሰው ከጎረቤቶቹ ጋር ከስራ ባልደረቦቹ ፣ ከመንፈሳዊ መሪዎቹ ወዘተ. ጋር መስተጋብር ያደርጋል፡፡ በሰው ቅርበት እና ርቀት ያነጋገር ስልቶቻቸውን በባህላዊ እና ማህበራዊ ስረአቶች እያገናዘቡ ንግግር ያደርጋሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች በተለያዩ ሁኔታዎች እና ስሜዎች ውስጥ ሆነው ንግግር ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ መለትም ሰው በገበያ ፣ በሱቅ ፣ በትምህርት ቤት፣በማምለኪያ እና በመሳሰሉት ቦታዎች ላይ ከሌሎች ጋር መስተጋብር ይኖራቸዋል፡፡ የፍረሀት ፣ የጭንቀት ፣ የስጋት ስሜት ሲያድርባቸው ስሜታቸውን ለሌሎች ማጋራት ይፈልጋሉ፡፡ ከግንኙነት አንጻር ደግሞ አዛዥ እና ታዛዥ ፣ ከሳሽ እና ተከሳሽ ፣ አስተማሪ እና ተማሪ እንዲሁም ሌሎችን በመሆን ንግግር ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያየ ተራ ወስደው የንግግር ክሂላቸውን እንዲያደሳብሩ በመምህራን ይታገዛሉ፡፡

Larsen (1986) ንግግር አስፈላጊ የሆነበትን ዋና ዋና ነጥቦችን ያስቀምጣሉ፡፡ ከነዚም መካከል በተለያየ እርከን የሚገኙ ሰዎች ለምሳሌ፡- በእድሜ ለገፉ ፣ ለሀይማሆት አባቶች ፣ ለመንግስት ባለስልጣናት እና ለመሳሰሉት መልእክት ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም የግል ጉዳይን ከሰዎች ጋር ለመወያየት እና ሀሳብን ለመቀያየር ንግግር አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ንግግር ሀሳብን በስልክ ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል ጠቀሜታ አለው፡፡ እንዲሁም በርካታ የግል ጉዳዮችን ለማቃለል ሲባል በዘወትር የስራ እንቅስቃሴ ሁሉ ንግግር አስፈላጊ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሰዎች መካከል ሊኖር እንደሚገባው ቅርበት በተለየዩ የአነጋገር ስልቶች ፣ ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊ ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ስረቸዎችን በጠበቀ መልኩ ዘወትራዊ ንግግር ማድረጉ የተለመደ እና ዘላቂነተ ያለው አስፈላጊ ነገር ነው (በድሉ ዋቅ ጅራ ፣ 1996)፡፡

ይህ እንግዲ የሰው ልጅ ከቢጤው ጋር ሀሳብ ለሀሳብ ሲለዋወጥ በአብዛኛው በንግግር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ እና ሀሳባቸውን ለመግለጥ ሲፈልጉ ለመናገር ሲቸገሩ ይስተዋላሉ፡፡ ይህ ችግር ደግሞ አጥኚዋ በጥናቷ የምትደርስበት ይሆናል፡፡ ንግግር ስው የሚያስፈልገውን ነገር ብቻ በቀላሉ እና ባጭሩ ለመናገር እንዲችል የሚያደርገው ነው፡፡ የንግግር ቅደም ተከተል ቢፋለስ መጀመሪያውና መጨረሻው ይጠፋና ንግግሩ ውስብስብ ይሆናል ፡፡ ስለሆነም በቅድሚያ ተናጋሪው ቃላትን በተገቢ መንገድ ማሳካት ተገቢ ነው፡፡ ተክለማሪያም ፋንታዬ (1964)፡፡

## 2.3. የንግግር ትምህርት አስፈላጊነት

ሰው ምንም ዝግጅት ሳያደርግ ባጋጣሚ ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ለመናገር ይገደዳል፡፡ ስለዚህ ሰው ለመናገር ዝግጅት ባያደርግም አጋጣሚዎች ሲያስገድዱት መናገሩ አይቀሬ ነው፡፡ መናገር ካለበት ደግሞ የተናጋሪውን ህብረተሰብ የቋንቋ ፣ ስረአት ፣ ባህል ፣ ስነ-ልቦና ፣ማህበራዊ እሴት ፣ በልምድ ወይም በትምህርት ማወቅ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የህብረተሰቡን ስሜት በማወቅ በንግግር መግለጽ ያለበትን ሀሳብ ሊያብራራበት ይችላል፡፡

Bygate (1987) ንግግርን ማስተማር ቸል የማይባል ጉዳይ መሆኑን ሲገልፁ በተለይ ተማሪዎች በራሳቸው የመተማመን ስሜት በማዳበር በሚያደርጉት ንግግር የእለት ተእለት ተግባራቸውን ማከናወን ይፈላጋሉ፡፡ በንግግር ጓደኝነትን ሊመሰርቱ ወይም ሊያጡ ይችልሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ንግግር አመርቂ የሆነ ማህበራዊ ትብብር ፣ ቦታ ወይም ከበሬታ መመስረቻ መንገድ ከመሆኑ በተጨማሪ ቋንቋን ለመማርም ሆነ ለማስተማር በመሳሪያነት በማገልገል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ይሁን እንጂ ኢ-አፈ ፈት የሆኑ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማስቻል ግን ቀላል ነገር አይደለም፡፡

Mc .Donalgh,Jo.and Shaw.Ch.(1995: 124) “ንግግር አስፈላጊነት ያለው የሌላን ሰው ድጋፍና ምክር ለማግኘት ፣ የሰው እርዳታ ሲያስፈልገን ፣ ለተለያዩ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ለመግለጽ እና ለኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ሲባል የንግግር ትምህርት አስፈላጊ ነው? ይላሉ፡፡ መናገር ሲያስፈልግ መናገር እንዲችሉ ደግሞ ለዛግጅት የሚያበቃ መሰረታዊ እውቀት ለተማሪዎች መስጠት ይገባል፡፡

ንግግር ከመልዕክት ማስተላለፊያ ኪሂሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን መልዕክትን ለማስተላለፍ ጊዜ የማይወሰነው ነው፡፡ እውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር የሚያስችል ኪሂል ነው፡፡ ተማሪዎች በመጀመሪያ ወደ ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት በአካባቢያቸው ከቤተሰብ ጋር በመግባባት ሂደት የሚያዳብሩት የቋንቋ ኪሂል ነው፡፡ ለዚህም ተግባር የንግግር አስፈላጊነትን እንዲረዱና በቀጣይ ከማንኛውም ኪሂል ጋር በጥምረት እንዲገለገሉበትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረጉ ኪሂሉ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጡትና የሚሰጣቸውን ትምህርት በአግባቡ እንዲከታተሉ ያደርጋል፡፡ የንግግር ትምህርት በማንኛውም የትምህርት አይነት ውስጥ አይቀሬ የሆነ ኪሂል ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪው ንግግርን ለምን ማድረግ እንዳአስፈለገው ማወቅ፤ ለማን እንደሚናገር መለየት እና እንዴት መናገር እንዳለበት በማወቅ በኪሂሉ መጠቀምና እውቀቱን ማዳበር ይጠበቅበታል፡፡

በአጠቃላይ የንግግር ትምህርት አስፈላጊነትና ተደራሽነቱ ወይም አገልግሎቱን በመረዳት ከሌሎቹ ኪሂሎች አቀራረብ ባልተናነሰ ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑና ለዚህ አላማ መሳካት የመምህራኑ ጥረት በዋናነት የሚታይ ጉዳይ ቢሆንም ተማሪዎቹም ስለ ጉዳዩ አጽንኦት እንዲሰጡትና አስፈላጊነቱን ተረድተው ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## 2.4. በክፍል ውስጥ የንግግር ኪሂል ትምህርት ወቅት የመምህሩ ስራና ሀላፊነት

ማስተማር ማለት የአንድን ነገር ክንውን ወይም አሰራር ማሳየት ወይም ለመስራት መርዳት ፤ መመሪያ መስጠት፤ ለማወቅና ለመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር ምክንያት መሆን ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች በመሆናቸው የመምህሩ ስራ መማር የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡ ለዚህም መምህሩ ስለ መማሪያ ክፍሉና በመማሪያ ክፍል መከናወን ስለሚገባው ሁኔታ ንግግር ከአእምሮአዊ ተግባር ስለመሆኑና በክፍል ውስጥም ሊከወን ስለመቻሉ ተገቢውን ግንዛቤ ማዳበር አለባቸው፡፡ መምህሩም ተማሪዎቹ የንግግር ኪሂሉን ጥቅም ተገንዝበው እንዲለማመዱ እና እንዲጠቀሙበት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በምሁራንም እንደተገለጸው የመምህሩ የማስተማር ችሎታ በተማሪዎች ትምህርት አቀራረብ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ጠቁመው የትኛው አቀራረብ /ስልት/ የተሻለ እንደሆነ ለይቶ መናገር ግን ቀላል እንዳልሆነ ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የንግግር ኪሂል ትምህርትን ለማስተማር ወደ ክፍል የሚገባ መምህር ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በጥሩ የማስተማር ዝግጅትና የንግግር ትምህርት አላማዎች ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ይዘቶችን በተገቢው የማስተማር ስነ-ዘዴ ለማቅረብ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው ስለሆነ በሚገባቸውና መገንዘብ በሚችሉበት ደረጃ ትምህርቱን ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም በንግግር ሀሳባቸውን በትክክል በተገቢው የቋንቋ ህግጋት መሰረት ለመግለጽ የሚያስችላቸውን እውቀትና ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማድረግ መምህሩ የትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ለመገንዘብ አጥጋቢ ስራ መሰራት አለበት፡፡

## 2.5. የስህተት ምንነት

Brown (1994 ፣ 206) ስህተትን ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች አንድ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተዎች የሚታዩበት፣ የታዩት ስህተዎች የሚተነተኑበት እና የተተነተኑት የስህተት አይነቶች በተለያዩ የምድብ አይነቶች ተከፋፈለው የሚቀመጡበት ዘዴ ነው፡፡

የስህተት መከሰት መንስኤ ከሚሆኑት ምክንያዎች ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ዘዴ አንዱ ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን በክፈል ውስጥ በንግግር ሲጠቀሙ

በተለያዩ ምክንያቶች ስህተት ሊፈጽሙ መቻላቸው የሚጠበቅ ነው፡፡የስህተቶች ምንነት እና ምንጮች የተለያዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ቁምነገሩ ይህንኑ አውቆ ተማሪዎች ከስተታቸው እንዲማሩ ጥረት ማድረጉ ላይ መሆኑን (Little wood ፣ 1984) ይገልጻሉ፡፡ አብዛኞቹ መምህራን ስህተት ከተሳታፊ ተማሪ ድክመት (ጥላቻ) የሚመጣ አድርገው ይገምታሉ፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እንደጉድለት የሚቆጠሩ እና መወገድ ያለባቸው መሆኑን የሚያምኑ መምህራን ይኖራሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ተማሪዎች ስህተት ወይንም ግድፈት ፈጽሞ ላለመፈጸም አበክረው ሊጥሩ ይችላሉ፡፡

Little wood. W.T(1986: 225)፣ Norrish.John.(1990፣1 ) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚው ቋንቋ በሚማሩበት ግዜ የሚፈጽሟቸው ግድፈቶችና ስህተቶች በተመለከተ ሁለት የተለያዩ መሰረታዊ አመለካከቶች አሉ፡፡ አብዛኛው መምህር ስህተት ከተማሪው ድክመት የሚመጣ እድርገው የቆጥሩታል፡፡ ይህም ተማሪዎች ትምህርቱ በሚቀርብላቸው ጊዜ በደንብ ካለማዳመጥ ፣ ለትምህርቱ ትኩረት አለመስጠት ፣ ከመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ እና ተማሪዎች በቋንቋው እሚለማመዱበትን በቂ ግዜ ካለማግኘት የተነሳ እንደሆነ ይገልጻሉ የቀሩት ደግሞ ስህተት ወይም ግድፈት መፈጸም የትምህርት አክል አድርገው ይቆጥሩታል በመሆኑም ስህተት እንደ ድክመት ምልክት ተደርጎ መታየት የሚገባው ሳይሆን የተማሪው የቋንቋ ለመዳ ስረአታዊ እድገት እና ተማሪዎች ቋንቋውን በሚጠቀሙበት ጊዜ ያለው ሂደት እንዴት እንደሆነ ምልክት የሚያሳይ ነው፡፡

ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት የሚፈጸሙት ስህተቶች እንደ ጉድለታ የሚቆጥሩና መወገድ ያለባቸው መሆኑን በሚያምኑት ዘንድ ተማሪዎቹ ስህተት መፈጸማቸው በመምህሩም ሆነ በተማሪዎቹ ዘንድ ዋጋ የሚያሳጣ ተደርጎ የሚወሰድ ስለነበር በርካታ ስህተቶችን መፈጸማቸውም ተግሳጽንና ቁጣን ያስከትልባቸው ነብር፡፡

በዚህ የተነሳ ተማሪዎች ስህተትን ወይም ግዲፈትን ላለመፈጸም ይፈራሉ፡፡ የፈረሀታቸው ምንጭም ተማሪዎቹ ስህተት(ግድፈት) በሚፈጽሙበት ግዜ በቋንቋ አፈ-ፈቺ ተማሪዎች ፣በክፍል ጓደኞቻቸው እና በመምህራኖቻቸው ዘንድ ይሳቅብናል ፣ ይቀልዱብናል ከሚል ፍረሀት የተነሳ በትምህርቱ እና በተማሩዎቹ ላይ ጥላቻ ያድርባቸዋል (Norrish,John.1990፣1)::

ሆኖም ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት በተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶች እንደጉድለት ሳያሆን የትምህርቱ አካል እንደሆ ተደርጎ መወሰድ የሚኖርበት ነው፡፡ በዚህ ረገድ Lindman (1996) ስህተት የመማር ሂደት አንድ አካል እና ትምህርቱንም በንቃት ለማካሄድ ጠቃሚ ምልከታ ነው ይላሉ፡፡ ተማሪዎች የሚሰሯቸው ስህተቶች ምንነት እና የመንስኤዎቻቸው ትንተና ታላሚውን ቋንቋ የመማር ማስተመር ሂደት ውጤታማ ሊሆን የሚችልበት አቅጣጫ ለማወቅ ያስችላል፡፡ በተለይም ለተማሪው ከስህተቱ እንዲማር መሳሪያ ሆኖ ማገልግል ስለሚችል ጠቀሜታውን የጎላ ያደርገዋል፡፡

በተጨማሪም Lindman (1996) ስህተት ቀደም ሲል በልማዳዊ ሁኔታ በተለያዩ ምልክቶች / ቃላትን ባለማወቅ ብነቃት ባለመከታተል ሀሳበ ብኩን በመሆን ወይም የእውቀት ማነስ /ከትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀም ማፈንገጥ እንደሆነ ተደርጎ ይገለጽ ነበር፡፡ ሆኖም በውጪ ቋብቋዎች ተማሪዎች ላይ ከተካሄደው ምልከታዊ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከታላሚው ቋንቋ አገባብ አለማፈንገጥም ስህተት ላለመፈጸም ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ ለምሳሌ የጀርመኒኛ ቋንቋ የሚማር አንድ ኖርጂኒያዊ ተማሪ በሰዋሰው በኩል ትክክለኛ የሆነ ዓረፍት ነገር ሊመሰርት ይችላል፡፡ ነገር ግን ስለጻፈው ጉዳይ እንደገና ዓ.ነገር እንዲጽፍ ቢጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ከበፊቱ የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ በእያንድ አንዱ የቋንቋ ተማሪ የሚፈጸሙ ስህተቶችም የተማሪውን እድገት አመልካቾች እንደሆኑ ተደርገው መቆጠር አለባቸው፡፡

እንደ Lindman እምነት ተማሪዎች በቋንቋ ላይ ካላቸው አጭር እና ረጅም ግዜ ግብአትና አጠቃቀም በመነሳት ለታለሚው ቋንቋ ስረአት መላ ምታቸውን እየመሰረቱ ይሄዳሉ፡፡ መምህራን ግን በቋንቋው ለመዳ ሂደት ተማሪዎቹ የሚያመነጯቸውን ነገሮች አውድ በማየት ስህተቶቹን ካልገመገሙ በስተቀር ተማሪዎቹ ላይ ይህን ማድረግ ይኖርባቸዋል ብለው ብያኔ ሊሰጡ አይችሉም፡፡ ስለዚህም የዚህ አይነቱ ግንዛቤ ሊኖር የሚችለው መምህራኑ እና ተማሪዎቹ በተማሩዎቹ ደረጃ በመምጣት እና የተማሪዎቹንም ባህሪ ለማጥናት ሰፊ ምልከታ የሚያካሂዱ እስከሆነ ድረስ ነው፡፡

በክፍል ውስጥ በተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶችን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለየዩ ብያኔዎችን ሲሰጡ ይስተዋላሉ፡፡ እንደ Dulay (1982) እና Brown (1994) እምነት ፣ ማንም ቢሆን የአፍ መፍቻም ሆነ ሁለኛ ቋንቋን ለመለማመድ ጥረት ሲያደርግ ስህተት

መፈጸሙ የግድ ነው:: ሆኖም ከተፈጸመው ስህተት በመማር ቋንቋውን ይለምሰዳል:: ከዚህም የተነሳ በቋንቋው ሂደት ውስጥ ስህተት የግድ ነው ብሎ መነሳት ይቻላል:: በስህተት እና በግድፈት መካከል ያለው ልዩነት በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ሰዎች ዘንድ የተለያዩ ስያሜዎች ሲሰጡ የቆየ ሲሆን ከነዚህም መካከል Norrish (1990:1) ከተለመደው ቋንቋ አጠቃቀም ውጭ ካሉት ባህሪያት/ ማለትም በስህተት ፣ በግድፈት እና በንግግር መሀል የሚፈጸም ትንሽ ስህተት /መካከል ያለውን ልዩነት መለየቱ ጠቀሜታ እንዳለው ያስገነዝባሉ:: ስህተት ከተለመደው ከቋንቋ አጠቃቀም ውጭ ስረአታዊ በሆነ ሁኔታ ማፈንገጥ ማለት ሲሆን ይህም ተማሪው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ያልሆን ነገር በመማሩ የሚፈጽመው ነው::

ተማሪዎች በንግግር ግዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት የሚሆኑት ነገሮች ምን እንደሆኑ አጥኝዎቸ ሲያስቀምጡ በዋናነት እንደ Brown (1994)፣ Little Wood (1986)፣ Norrish (1993) ፣Dulay(1982) የስህተት ምንጩች ካሏቸው መካከል የመማር ማስትመር ችግር፣ የስነ- ልቦና ችግር እና የውስጥ ቋንቋ ተጽኖ በዋናነት ይጠቀሳሉ::

## 2.6. የንግግር ስህተት ትንተና

የስህተት ትንተና ለታላሚው ቋንቋ ለመማር ማስተማር ሂደት የበለጠ ውጤታማ የሚሆንበትን አቅጣጫ ይጠቁማል:: ይህን ሀሳብ በተመለከተ Lott (1983፣ 256) Jackson.H.(1987 ፣102) እና Dulay.et.al.(1982፣ 138 -139) ሲገልጹ የስህተት ትንተና ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ያላቸው እውቀት ምን ያህል እንደሆነና ጠንክረው ቢሰሩ የትኞቹን ስህተቶች በቀላሉ እንደሚያሶግዱ ፣ እንደዚሁ በየትኛው የታላሚ ቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተው መለማመድ እንደሚገባቸው ይጠቁማል::

በተጨማሪም የስህተት ትንተና ፣ አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማር ተማሪ ከሚፈጽማቸው ስህተቶች በመነሳት ተማሪው ስለታላሚው ቋንቋ ያለውን ችሎታ ለመገምገም ስለሚችል ፣ ስለተማሪው የተሸለ መረጃ ለመስጠት ያገለግላል:: ይህም ተማሪው የትኞቹን የቋንቋ ይዘቶች በይበልጥ መማር እንዳለት ይጠቁማል:: እንዲሁም የሚፈጽማቸውም ስህተቶች ከስነ ልቦናዊ ክፍሎች አኳያ ከፋፍሎ በማስቀመጥ በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙትን መሰናከሎች ለመለየት ይጠቅማል:: Samuel (1987፣ 102):: በአጠቃላይ ለመምህራን የተማሪዎችን ችግር በመጠቆም የትኩረት

አቅጣጫን በማሳየት የማስተማርያ መሳሪያዎችን እና የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዲፈትሹ በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡ በሌላ መልኩ የስህተት ትንተና ለመምህራን ከሚኖረው ፋይዳ በተጨማሪ ለቋንቋ ተማሪው ፣ ለቋንቋ ተመራማሪዎች እና ለመረሀ ትምህርት አዘጋጆች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ Richards (1974 ፣25) ፣Corder (1974 ፣257) ፣Norrish (1983፣ 86) Olsen (1991 ፣ 191) እና Lengo (1995፣ 20-21) እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

- ለተማሪው ከስህተቱ እንዲማር እንደመሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህውም የታላሚውን ቋንቋ ህጎች ለመግለጽ ሚጠቀምባችውን ግምቶችና መላ ምቶች በተግባር ለማረጋገጥ እና ለመፈተሽ ያስችላቸዋል፡፡
- ለቋንቋ ተመራማሪዎች አንድን ቋንቋ እንዴት መማር እንደሚቻል እና ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚጠቀምባችውን ብለሀቶች እና ቅደም ተከተሎች በተመለከተ መረጃ በምስጠት ያገለግላል፡፡
- ለመረሃ ትምህርት ቀራጨች እና ለማስተማሪያ መስሪያ አዘጋጆች መረጃ በመስጠት በመረሀ ትምህርቱ እና በማስተማሪያ መሳሪያዎቸ ውስጥ የትኞቹ ይዘቶች ቅድሚያ መሰጠትና መደራጀት እንዳለባቸው ግንዛቤ ያስጨብጥል፡፡

የስህተት ትንተና ከላይ የተዘረዘሩት ጠቀሜታዎች ቢኖሩትም ፣ በአንድ ግዜ ብቻ በሚካሄድ ጥናት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንዲህ አይነት ስህተት አለባቸው ብሎ አጠቃላይ ድምዳሜ መስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Sharma (1986 ፣77-78) በአንድ የትምህርት መረሀ ግብር መነሻ መካከልና መጨረሻ የስህተት ትንተና የሰው ልጅ ንግግር ሲያደርግም ሆን ነገሮች አስገድደውት ሲናገር ከንግግር ጋር የተያያዙ ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ተግባሩን ከመሰሉ ጋር የሀሳብ ልውውጥ ሲያከናውን በንግግር ውስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች አሉ፡፡ እነዚህም ስህተቶች የድምጽ ፣ የቃላት ፣ የሀረጋትና የዓ.ነገሮች መዋቀራዊ ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ የስተት ምንጮች ትንተና ምንምን እንደሆኑ በአጥኚዋ ይፈተሻሉ Thompson, Anne. (1991) በንግግር የሚፈጸሙ ስህተቶች የሚሏችው የሰዋሰው ሂደት አለመጣጣም ፣ ለማን መንገር እንዳለበት አለማወቅ ፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች በይበልጥ

ጎልተው ይታያሉ ይላሉ፡፡ በመሆኑም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲግባቡ የሚፈጥሟቸው ስህተቶች የሚስተዋሉ ናቸው፡፡

በቋንቋ የመማር ማስተመር ሂደት ተማሪዎች በንግግር ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ልምምድ ወቅት በታላሚው ቋንቋ የፈቱትም ሆነ ኢ-አፈ ፈት የሆኑ ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶች ይፈጽማሉ፡፡ ነገር ግን የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ለተማሪዎቹ የቋንቋ እድገት አስተዋጾ የሚያደርጉ እንጂ የውድቀት ምልክት እንዳልሆኑ የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ይገልጻሉ Little Wood (1984):: ከእኚህ ምሁር አባባል የምንገነዘበው ጉዳይ ተማሪዎች ቢሳሳቱም ስህተታቸው እንደ ትምህርት ተቆጥሮ ማበረታታት እንጂ ተማሪውን ትክክል አይደለህም ብሎ ማስደንገጥ አላስፈላጊ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 2.7. የንግግር ክሂል ሲማሩ የተማሪዎች ድርሻ

የንግግር ኪሂል ተማረዎች ሲማሩ ሰፋ ያሉ ችግሮች ሊገጥሟ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ ይህም ሊከሰት የሚችለው ኪሂሉን ለማስተማር ከሚዘጋጁት ግብአቶች አንስቶ የአቀራረብ ችግር፤ የመምህራን ችሎታ፤ ከተማሪዎች የትምህርት አቀባበልና አመለካከት ፍላጎት፤ ተማሪዎች እንደሚሳሳቱ በማሰብ ለመጨነቅ ለመናገር መሞከርና ፈጽሞ ለመነገር ያለመሞከርና የመሳሰሉት ጉዳዮችን ለአብነት መግለጽ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች እነኝህን ችግሮች አስወግደው የንግግር ኪሂልን በድፍረትና በፍላጎት በተሞላው መንፈስ ሁል ጊዜ ንግግርን እንዲለማመዱ ማበረታታት እና ፍርሀትን አስወግደው ጥሩ ተናጋሪ እንዲሆኑ ማበረታት ይገባል፡፡

Brown (1994፤206)የስህተት ትንተና ማለት ተማሪዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ ለሚፈጽመዋቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣ የሚታዩት ስተቶች የሚተነተኑበት የተተነተኑበት የስህተት አይነቶች ለተለያዩ የምድብ ዐይነቶች ተከፋፍለው የሚቀመጡበት ዘዴ ነው፡፡

## 2.8. የንግግር ኪሂልን ትምህርትን አዳጋች የሚያደርጉ ነገሮች

የተለያዩ የስህተት ምንጮች እንዳሉ በተለያዩ መልክ ተጠቅሰዋል፡፡ ስለሆንም ለዚህ ጥናት ተከታይ ክፍል ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የተገሙቱትን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 2.8.1.የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ

Brown (1994፣206 እና 213-214) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በመጀመሪያ ደረጃ መለያ ባህሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ወይም ጣልቃ ገብነት ነው፡፡የስህተት ትንተና የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ሽግግር ብቻ ሳይሆን ሊሆኑ ከሚገባቸው የስህተት ምንጮች አንፃር ስህተቶችን የሚመረምር በመሆኑ ከንጽጽራዊ የስህተት ትንተና የተለየ ነው፡፡

Norrish (1990፣41-42) የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት በአሁኑ ሰዓት  የሚኖረው ሚና አነስተኛ መሆኑን ቢገልጹም ለስህተት መፈጠር ምክንያት እና ጠቀሜታ ያለው መሆኑ አልካዱም፡፡ ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋ መግባባት ቢፈልግና የዚያን ቋንቋ ተገቢውን አገላለጽ እና የቋንቋ መዋቅር በሚገባ ባያውቅ የግዴታ ሀሳቡን ለመግለጽ ሲል ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋው መሄዱ የግድ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ስህተትን ይፈጽማሉ ቋንቋ ማለት ይሔነው  ተብሎ በቀላሉ የሚገመት ሳይሆን ማለቂያ የሌለው ተማሪው ቋንቋውን  ከተማረው በኋላ በቋንቋው ቢጠቀም በሚፈልግበት ጊዜ ማለትም ሲናገር ወይም ሲጽፍ ያልተማረውን ወይም ያልፃፈውን በመጻፍ ስህተት ይፈጽማል፡፡ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያቱ ተማሪው በክፍል ውስጥ ለተጋለጠበትና  ይማረዋል ተብሎ በታሳቢው ቋንቋ የሚወሰን ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ለሚፈጽመው ስህተት ምክንያቱ ተማሪው በክፍል ውስጥ የሚያጋጥመው ተጽእኖ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

Nagara(1983፡36) ለቋንቋ ችሎታ ስህተቶች ዋና የስህተቱ ምንጭ የሚሆነው እንደተለመደው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ሲሆን የአሁኖቹ ጸሀፊዎች "አፐሮክስሜሽን"  ብለው የሚጠሩት ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ታመሪዎች የአፍመፍቻ ቋንቋቸው ባህሪ ጋር  ተመሳሳይ በሆነ ወይም ግምታዊ በሆነ ሙከራ ቋንቋውን ያፈልቃሉ፡፡እነዚህ "አፐሮክስሜሽኖችም" ከታላሚው ቋንቋ ትክክለኛ ቅርጽ ያፈነግጣሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡

### 2.8.2. የውስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ

ሌላው የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ የሚታወቀው አሉታዊ ውስጠ ቋንቋ ሽግግር ስህተት ብያኔ የሚባለው ሲሆን ይህም አንድ ግዜ ተማሪው የ2ኛ ቋንቋውን አዲስ ስርአት ከለመደ በኋላ በታላሚው ቋንቋ በይበልጥ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ስህተት የሚመጣ ነው፡፡ Brown;(1994:214)እና little wood(19986፡23) ይህንን በተመለከተ Negara (1983፣36)

ለውስጥ ቋንቋ ስህተቶች መፈጠር ምክንያጽ የሆነው ጉዳይ በርካታ ሙሁራን "ስህተት ብያኔ" ብለው እንደሚጠሩት ከገለጹ በኋላ በውስጥ ቋንቋ ስህተቶች መነሻ የሆኑት 3 ጠቃሚ የሆኑትን ጉዳዩች አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህም ፡- ያልተሟ ትምህርት፣ የተሳሳተ ቅንጅትና ያአግባብ ቃላትን መጠቀም ናቸው በማለት ይገልፆቸዋል፡፡

"Negara" የስህተት ብያኔ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያብራራ ተማሪ በታላሚው ቋንቋ ያወቃቸውን የቋንቋ ህጎች ወይም የስነ ልሳን ጉዳዮች በማይመለከተው ስፍራ ወይም ተገቢ ባልሆነ አውድ ተግባራዊ ማድረግ እንደሆነ ከጠቆሙ በኋላ ይህም በቋንቋ ውስጥ ያለው አጠቃላይ ህግ በማስፋፋት የመጠቀም ጉዳይ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ያልተሟ ትምህርት ስህተት የሚባለው የተለየ ዘርፎች ያለው ሲሆን

እነዚህም ፡- 1 ያልተሟላ የሰዋሰው ህግ አደረጃጀት

2. ያልተሟላ የመስተዋድድ ሀረግ ትምህርት

3. ያልተሟ የቋንቋ አገላለጽ ትምህርት

4. ፍቺውን (ትርጉሙን) በቀላሉ ለመለየት ወይም ለገንዘብ ያልተቻሉ ቃላት አይነት ናቸው፡፡

## 2.8.3. ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች

Norrish (1990፣19) ቀደም ሲል በተጠቀሱት የስህተት ምንጮች በተጨማሪም ተማሪዎች ስህተቶችን እንዲፈጽሙ የሚያደርጓቸው ስነ ልቦናዊ ምክንያቶች እንዳሉ ነው፡፡ ስነ ልቦናዊ ጉዳይ ሲባሉ የሚያያዘው ከተማሪዎች ግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን ይህም ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ስላለው ሁኔታ በአዕምሯቸው ውስጥ ይዘውት የመጡት ጉዳይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዲከታተሉ ስለያደርጋቸው ነው፡፡ የእነዚህ አይነቶቹ ስህተቶችም በ "corder" ያላስፈላጊ ድግግሞሽ ተብለው መጠራታቸውን ይገልጻሉ፡፡ እነዚህም ስህተቶች ከቋንቋ መማር ጠቃሚ ክፍሎች ከሚጠሩት ስህተቶች የተለዩ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡ ሙሁራን ስለ ስህተት ምንጮች በሚጠየቁበት ግዜ የሚሰጧቸው መልሶች ተቀራራቢነት ያላቸው ቢሆኑም አንዳነዶቹ ከተማሪዎቹ ግዴለሽነት የሚመጣ ነው ማለታቸውንም፡፡ Norrish ገልጸውታል፡፡

እንደ Norrish አባባል ግዴለሽነት ብቻውን ለስህተት መፈጠር ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን ተማሪዎቻቸው ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት እንደሆኑ አድርገው ይወስዱታል፡፡ ግዴለሽነት ለመማር ካለ ፍላጎት መቀነስ ጋር በቀጥታ ይገናኛል፡፡ ይህም ፍላጎት ማጣት ምን አልባትም የትምህርቱ አቀራረብ ወይም ለትምህርቱ የቀረበው ነገር ከተማሪው ባህሪ ጋር አለመስማማቱ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በግዴለከሽነት የሚፈጸውን ስህተት ለመቀነስ የሚያስችለው መንገድ አንዱ የእርስ በእርስ እርማትን ማካሄድ እንደሆነና የዚህ አይነቱ የአስተራረም መንገድም ስህተቶችን የመመርመር ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደሆነ Norrish ገልጸውታል፡፡

### 2.8.4.ሰዋሰዋዊ ችግር

እንደ BYme (1997) አባባልም በንግግር ወቅት ገለጻ ስናደግ አድማጭ ንግግራችንን እንዲቀጥል ያግዘናል፡፡ ንግግራችን ላይ ችግር (ስህተት) ቢፈጠር እየደገምን ወደ በኋላ እየተመለስን መቀጠል እንችላል፡፡ ነገር ግን በንግግራችን ወቅት የሰዋ ሰው ስህተት ካለበት አድማጩ የንግግሩን መልዕክት አለመረዳት ሊያጋጥመው ይችላል፡፡ በመሆኑም የሰዋሰው ስህተቶችን በመለየትእና የስህተቱን ምንጭ ምንድ ነው? የሚለውን ነጥብ በጥናቱ የተመለከትኩበት ነው፡፡ Thampson /anne(1991) በንግግር ወቅት የሚፈጸሙ ስህተቶች የሰዋሰው ሂደት አለመጣጣም፣ ለማን መናገር እንዳለበት አለማወቅ፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በይበልጥ ጎልተው ይታያሉ ይላሉ፡፡ ንግግር መደረግ ያለበት በሌላ ወገን መልዕክት ለማስተላለፍ እስከሆነ ድረስ አቀራረቡ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያፈርስ መሆን የለበትም ወይም ሊሆን አይገባም፡፡ ስለዚህ ለማን፣ ምን፣ መቼ፣ እንዴት ወዘተ መናገር እንዳለበት ተማሪዎች በተለመዱ በዕድሜ ሲገፉ እና ተለያዩ ሀላፊነቶች ሲቀበሉ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት ሀሳብን ለመምረጥና በማደራጀት ፣ አድማጭ ለማወቅ፣ የሚነገርበት አውድ ለመለየት፣ እንዲሁም ተስማሚ አገላለጽን በመጠቀም ንግግር ማድረግ ይለምዳሉ፡፡

በዚህ አንጻር የንግግር ክሂል ማወቅ ወይም መቻል ማለት በንግግር ሀሳብን በንቃት መግለጽ ማለት ነው፡፡ ሀሳብን አፍ እንዳመጣ ከመናገር ይልቅ የቋንቋው የሰዋሰው አገባብ ወይም አጠቃቀም መረዳት ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች አፋቸው ባልፈቱበት ቋንቋ ብዙም በንግግር ሲሳተፉ አይታዩም፡፡

ንግግርን ለማረም የሚጠቅሙ ነገሮች ውስጥ አንዱ ንግግር በሚደረግበት ስፍራ መሄድ እና መስማት ፤ ሌላው ደግሞሬድዮ ማዳመጥ እና ንግግር በማድረግ መለማመድ ጠቃሚ ነው፡፡ ተክለማሪያም ፋንታዬ(1964)፡፡ ስለዚህ ከአንደበታችን የሚወጣው ድምጽ ስርአትን ተከትሎ አድማጭ ጆሮ ገብቶ ምላሽ የሚሰጥበት ወይም መልዕክት የሚተላለፍበት ስለሆነ ሰዋሰዋዊ ሂደት ተከትሎ መቅረብ ይገባዋል ማለት ነው፡፡

## 2.9 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የቀደምት ጥናቶች ቅኝት የሚለው ክፍል ዓላማ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የቀደምት የጥናት ሥራዎች የሚቃኙበት ነው፡፡

ውድአዲስ ምህረቱ (2001) አማርኛ ቋንቋ በማስተማር ሂደት መምህራን ለማዳመጥ እና ለንግግር ኪሂሎች የሚሰጡት ትኩረት በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ የመሰናዶ ት/ቤቶች 11ኛ ክፍል ናሙናነት ባደረጉት ጥናታቸው መምህራን ካላይ ለተጠቀሱት ኪሂሎች በቂ ትኩት ያለመስጠታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ይህም የማዳመጥ ኪሂል በመረሀ ትምህርት ውስጥ በአጠቃላይ እና በዝርዝር ዓላማው እንዲሁም በይዘቱ ከንግግር ኪሂል ጋር ተደምሮ በቅረቡ ለመመህራኑም ሆነ ለመማሪያ መጽሀፍት አዘጋጆች በየትኛው ኪሂል ላይ ማትኮር እንዳለባቸው ያለማመልከት ችግር እንደሚታይበትና የተሰጠውም ትኩረት አነስተኛ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ጥናቱ ከዚሀ ጥናት ጋር የንግግር ኪሂል ማንሳቱ ላይ ተመሳሳይነት ቢኖረውም ከሚያነሳ ትኩረት ነጥብ አኳያ የተለየ ነው፡፡

እጅጉ ይማም (2003) የጥናታቸው አላማ በደብረ ብርሀን ከተማ በተመረጡ 3 አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ7ኛክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ኪሂል አቀራረብን መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱም ውጤት የመምህራን የማነገር ክሂል አቀራረብ እና ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመድሱን አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም የ7ኛ ክፍል አፈፈ ፈት ተማሪዎች ላይ መምህራን የንግግር ኪሂልን ሲተገብሩ አብዛኞቹ ተማሪዎች ሀሳባቸው በትክክል ያለመግለጽ ችግር እንዳለባቸው መምህራንም በኪሂል ትግበራው ላይ ችግር እንዳለባቸው በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

ይህ ጥናት ደግሞ ኢ-አፈፍት ብቻ የሚመለከት እና ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ንግግርን ሲማሩ የሚፈጽመዋቸውን ስተቶች መፈተሽ ስለሆነ ልዩነት አለው፡፡ የንግግር ኪሂልን በማንሳቱ ቢመሳሰልም ይዞት የተነሳው የትውኩረት አቅጣጫ ልዩነት አለው፡፡

በአጠቃላይ  ከላይ የተዘረዘሩት የቀደምት ጥናት ስራዎች በማዳመጥእና በንግግር ኪሂሎች ላይ መሰረት ያደረጉና የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ የዓተገባበር ሂደት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚዋ ይዛ ከተነሳችው የጥናት ርዕስ ጋር በንግግር ኪሂል በኩል መሰረቱ ተመሳሳይነት ያለው  ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ  አጥኚዋ ይዛ የተነሳችው የጥናት ዓላማ ከቀደምት ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል፡፡    በመሆኑም  አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግርን ሲማሩ የሚፈጽሟቸው  ስህተቶች ምን ምን እንደሆኑ እና ለስህተቱም መከሰት ምንጩ ምን እንደሆነ?  በጥናቱ ለማየት ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ስልት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳደር በባሌ ዞን በጎባ ወረዳ በሚገኙ ሁለት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በኦሮምኛ ቋንቋ አፍቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንግግር ኪሒል ሲማሩ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፈተሸ ሲሆን መምህራንም ትምህርቱን እንዴት እንደሚተገብሩና በአተገባበር ወቅት የተማሪዎች አቀባበልም ምን እንደሚመስል በመለየት በአተገባበር ወቅት የሚያጋጥሙ ተግዳራቶች ለመለየት ድብልቅን የምርምር ዘዴን ተጠቅማለች፡፡ በአቀራረቡም ገላጭ የምርምር ስልትን በመጠቀም ከቃለ መጠይቅ ፣ የፅሑፍ መጠይቅና ከክፍል ምልከታ በምርምር የተገኘው ውጤት በትረካዊ ወይም በገለፃዊ መንገድ ተተትኗል፡፡

## 3.2. ተጠኚዎች

### 3.2.1 የጥናቱ አካባቢ

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በጎባ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ በወል-ተኢ ጢሎ እና በሲንጃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች በጎባ ወረዳ በስተ ምስራቅና ምዕራብ ከአራት እስከ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ደጋ የአየር ፀባይ ያላቸው ናቸው፡፡ የአካባቢውን ማህበረሰቦች ኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ ሁለቱንም ቋንቋዎች እና አማርኛ ቋንቋ ብቻ የሚጠቀሙም ይገኙበታል፡፡ እምነታቸውም እስልምና ፣ ክርስትና (የክርስትና እምነት) ተከታዮች ሲሆኑ ጥቂት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮችም ይገኛሉ፡፡ መተዳደሪያቸውም በከብት አርባታና በወተት ሽያጭ ፣ የጓሮ አትክልቶችንና የባህር የባህር ዛፍ ተክለው በመሸጥና በመሳሰሉት ስራዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

### 3.2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች

ይህ ጥናት የተካሄደው በባሌ ዞን በጎባ ወረዳ በ2013 ዓ.ም በወልተኢ ጢሎ እና በሲንጃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ አንድ ወንድ እና ሦስት ሴት በድምሩ 4 የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በተጠኝነት ያካተተ ሲሆን ፣ ለጥናቱ አጋዝነት በሁለቱ ትምህርተ ቤቶች ከሚገኙ 197 ወንዶች እና 215 ሴቶች በድምሩ 412 ተማሩዎች ውስጥ የጥናቱ ተሳታፊዎች 23 ወንዶች እና 25 ሴት በድምሩ 48 የ7ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ኢአፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎችን ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

### 3.2.3. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የዚህ የጥናት ዋና አላማ በጎባ ወረዳ በወልተኢ ጢሎ እና በሲንጃ አንደኛ ትምህርት ቤቶች በ2013 ዓ.ም የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንግግር ኪሒልን ሲማሩ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቀነስ የሚኖረውን ሚና መመርመር ነው፡፡ ይህንን ጥናት ለማካሄድ በጎባ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ 16 ት/ቤቶች ውስጥ የወልተኢ ጢሎ እና የሲንጃ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ካሉት 16 ት/ቤቶች ውስጥ ሁለቱ የተመረጡበት ምክንያት በአሁኑ ግዜ ተከስቶ ባለው የኮሮና ቫይረስ ምክንያት እንዲሁም ከትምህርት ቤቶች እርስ በእርስ መራራቅ የተነሳ ለጥናቱ አመቺነት ያለመኖሩ ነው፡፡ ሌላው የተመረጡት ትምህርት ቤቶች በጎባ ከተማ እና በገጠር ቀበሌዎች አዋሳኝ ሆነው ስለሚገኙ እና ተማሪዎች ከከተማ እና ከገጠር አካባቢም ስለሚመጡ ፣ ተማሪዎቹ የመጡበት ዳራ እና የቋንቋ አጠቃቀማቸው ለጥናቱ ጠቃሚ የሆነውን መረጃ ያስገኛል ተብሎ ተገምቶ ሲሆን አጥኚዋም በወልተኢ ጢሎ ትምህርት ቤት የምታስተምር በመሆኑ እና የማህበረሰቡን በህልና ወግ ስለምታውቅ ከሌሎች ትምህርት ቤቶች በተሻለ መረጃ ለመሰብሰብ እና ጥናቱን ለማካሄድ ያመች ይሆናል ብላ በማሰቧ ነው፡፡

### 3.2.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪዎቹ በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በጎባ ወረዳ በወል-ተኢ ጢሎ እና ሲንጃ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና የአማርኛ ቋንቋ ኢአፈ-ፈት የሆኑ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ለጥናቱ ኢ -አፈ ፈት የሆኑ ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት አጥኝዋ ካላት የረዥም ግዜ(15) ዓመት የማስተማር ልምድ በንግግር ኪሒል በአማርኛ ኢአፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በበለጠ አማርኛን ለመናገር ሲቸገሩ በማየቷ እና የዚህ ችግር መንስኤ ለመረዳት

ከማሰብ የመነጨ ሲሆን ፤ ሁሉንም ኢአፈ-ፈት ተማሪዎች ለጥናቱ ናሙናነት ያካተተችበት ምክንያት የመረጃ ሰጪ ተማሪዎች ቁጥር አናሳ በመሆኑ በአማርኛ ቋንቋ የአፈ-ፊት የሆኑ ተማሪዎች በሙሉ ከሌሎች ተማሪዎች በጥያቄ በመለየት ወልተኢ ጢሎ ት/ቤት ወንድ 13 ሴት 11 በድምሩ 24 ከሲንጃ ት/ቤት ወንድ 10 ሴት 14 በድምሩ 24 በአጠቃላይ ድምር 48 ተማሪዎችን በጠቅላይ የናሙናን ዘዴ በመጠቀም ተመርጧልና የናሙናው ቁጥር መጨመሩ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ማስረጃዎችን ለማግኘት ያስችላል ከሚል እሳቤ ነው፡፡ ለጥናቱ በተመረጡ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በሰባተኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ወንድ 23 ሴት 25 ድምር 48 ሲሆኑ ይህ አሀዝ የሚያመለክተው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ እና ኢአፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የሚያጠቃልል ሲሆን ፣ ወንድ 23 ሴት 25 ድምር 48 ከሁለት ት/ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ኢ- አፈ ፈት የሆኑ የመረጃ ሰጪ ተማሪዎችን ብቻ ይመለከታል ፡፡

### 3.2.5. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ1-8ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን በተመረጡት የሰባተኛ ክፍሎች የተማሪ ቁጥር ከሌሎች ክፍሎች የተሻለ በመሆኑ ፤ የአማርኛን ቋንቋ ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ በመሰጠቱ እና በተመረጠው ክፍል በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ የተዘጋጀው የንግግር ኪሒል ይዘት እና የተማሪዎች የመናገር ችሎታ ጥናቱ ይዞ የተነሳውን አላማ ለመፍተሽ ከ5ኛ እና 6ኛ ክፍሎች የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡ ከሚል እሳቤ እንዲሁም በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ በአማርኛ ቋንቋን ኢአፈ-ፈት ተማሪዎች ከተጠቀሱት ክፍሎች በበለጠ የሚገኙት በነዚህ ክፍሎች በመሆኑ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆነ መረጃን ለማግኘት የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡ ብሎ ከማሰብ የተነሳ ክፍሉ ሊመረጥ ችሏል፡፡ ይህንን ሀሳብ creswell (2012) ገለፃ መሰረት የአንድ ጥናት ተሳታፊዎች ተመሳሳይ በህሪያትን የሚናገሩ ቡድኖች ወይም የሰዎች ስብስብ ሊሆን እንደሚገባ የመለከታል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በማንኛውም ጥናታዊ ክንውን አጥኝዋ እንደ ጥናቱ በህሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ መሳሪያዎች ይኖሩታል፡፡ ያለው (2004 ፤ 147-148) ሲገልፁ የፅሁፍ መጠይቅ ፤ ቃለ መጠይቅ ፤ ምልከታ ፤ መዛግብት ክለሳ ፤ ፈተናዎች እና ውይይት ዋና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

ለጥናቱ አመቺ እና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ 4(አራት) አይነት የመረጃ መሰብሳቢያ መንገዶች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህም ምልከታ፣ ቃለ መጠየቅና የጽሁፍ መጠይቅ እና ፈተና ናቸው፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በዋናነት የተመረጠው የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲሆን ለጥናቱ በቂ መረጃ በማሰባሰብ እና የትምህትቱን አቀራቀብ ከምንጩ ለመረዳት ስለሚያስችል ነው፡፡ በምልከታው የተገኙ መረጃዎችን በማጠናከር እና ለመምህራን ለቀረቡ መጠይቆች እና ለተማሪዎች ለቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆች ከተሰበሱበት መረጃዎች የተሟላ መረጃ ለማሰባሰብ ከማሰብ በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱት አራት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 3.3.1 የመማሪያ ክፍል ውስጥ የትምህርት አተገባበር ምልከታ

የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ ከተመረጡ የመረጃ መሰብሳቢያ ዘዴዎች በዋናነት የክፍል ውስጥ የትምህርት አተገባበር ምልከታ ሲሆን ምልከታው ከመካሄዱ በፊት አጥኚዋ ቅጽ በማዘጋጀት እና በክፍል ምልከታው የተዘጋጁትን 11 ጥየቄዎችን በአማርኛ ትምህርት ክፍልና ልምድ ባላቸው መመህራን አስገምግማለች፡፡

ከአጥኚዋ ጋር በመሆን ምልከታውን በማድረግ በረዳትነት የተመረጡ መምህራን በአማርኛ ትምህርት ክፍል ውስጥ 22 ዓመት በላይ  ያገለገሉ እና የመምህራን የስራ አፈፃፀም ላይ የተሳተፉ ልምድ ያላቸው መምህራን በመሆናቸው ለምልከታው አሞላል ጥራት ያግዛል ተብሎ በመታሰቡ በመረጃ መሰብሳቢያነት እንዲሳተፉ ከምልከታው በፊት ስለ ጥናቱ አላማ፣ አስፈላጊነት እና አሞላል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ያለው (2001) እንደተገለፁት የመማሪ ክፍል ውስጥ የትምህርት አተገባበር ምልከታ ሲደረግ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ተከታታይ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡ ተመራማሪዋ ይህንን ዘዴ ስትጠቀም የምታጠናውን ባህሪ ረዘም ላለ ግዜ ትከተለዋለች፡፡ በክትትልም ወቅት የሚመለከተውና የሚስማማውን ባህሪ ትመዘግባለች፡፡

በዚህ መሰረት በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚስያተምሩበት ጊዜ ከርእሱ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ባለው ይዘት ላይ በመመስረት የመምህሩን የንግግር ኪሂል አተገባበር ተጠኚዎቹ እያንዳንዳቸውን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ 35 ደቂቃዎች አተገባበራቸውን በመመልከት ለየክፍለጊዜው በተዘጋጀው አንድ አንድ ቅጽ ላይ ምልከታው ከተካሄደ ቅጾቹ በመጠይቁ መሰረት ከተተገበረ ተተግብሯል፣ ካልተተገበረ ደግሞ አልተተገበረውም፣ ተብለው በተዘጋጀው ሰንጠረዥ ውስጥ ድርጊቱን የተገቡሩት መምህራኖች ብዛት በቁጥር ተሞልተዋል፡፡ እንደተጠኚዎቹ የንግግር ክሂል ትምህርትን ከዚህ በፊት በክፍል ውስጥ ሲተገብሩት እንደነበው አሁንም በነፃነት እንዲተገብሩ ለአራቱም መምህራን ከተገለፀላቸው በኋላ፣ በክፍለ ጊዜው የተገኘው መረጃ ለምልከታው ውጤት መሰብሰቢያ ከተዘጋጀው ቅጽ ላይ በምልከታ አድራጊዎች በየቅጾቹ የተሞቱትን የምክልከታ ውጤቶች ከምልከታ አድራጊው መምህር ጋር በመናበብ እና ውጤቶችን በማቀናጀት ለምልከታው ውጤት መሙያ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ተሞልቶ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

### 3.3.2 የጽሁፍ መጠየቅ

ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ለማግኘት ያልተቻሉ እና ለጥናቱ አጋዥነት ያላቸውን መረጃዎች በተጨማሪ ለመግኘት ያስችል ዘንድ ከተጠኚ ተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ የጽሁፍ መጠየቅ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ለመረጃ መሰብሰቢያነት የጽሁፍ መጠይቅ የተመረጠበት ምክንያት በመምህራኑ ቃለ መጠየቅና በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት በትክክል ያልተመለሱ ጥየቄዎችን ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታስቦና ለጥናቱ ጠቃሚነት ያላቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ የተማሪዎቹ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ከሌሎቹ መረጃ መሰብሰቢዎች በተሻለ መረጃዎችን በቀላሉ ለመሰብሰብ እና ለማጠናከር በመረጃ ሰጪዎቹን በነጻነት መረጃዎች ይሰጣሉ ተብሎ ስለታሰበ ዘዴው ተግባሪዊ ተደርጓል፡፡

ዋናው ጥናት ከመካሄዱ በፊት ለመረጃ መሰብሰቢነት ከተዘጋጁት የጽሁፍ መጠይቆች ውስጥ ከወልተኢ ጢሎ ትምህርት ቤት በቀላል እጣ ንሞና የተመረጡ 10 ተማሪዎች አምስት አምስት ተማሪዎችን በማደል እና ጥያቄዎችን እንዲፈትሹ በማድረግ እርማት የሚያስፈልጋቸውን ማለትም የረዝሙ ጥያቄዎችን በማሳጠር እና በቀላሉ የጥያቄውን ሀሳብ እንዲረዱት በማድገት፣ ለእያንዳዱ ጥያቄ መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ግልጽነት የጎደላቸው ጥያቄዎች ተብራርተው እንዲቀርቡ

በማድረግ እና የጥናቱ ጥየቄዎች በመፈተሽ በተመረጡ ተማሪዎች የሚታዩትንያልተስተካከለ እና ግድየለሻዊ መልስ አሞላሎች ለመፈተሽ ከቀረቡት ጥያቄዎች ከተቃኙት የስህተት ግብአቶች በመነሳት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

### 3.3.3. ቃለ መጠይቅ

ሌላው ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት በአጥኚዋ ስራ ላይ ያዋለችው ዘዴ ቃለ መጠይቅ ሲሆን መመህራን የንግግር ኪሂልን ሲተገብሩ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች እንዴት እንደሚተገብሩ ለመረዳት አስተያየት እና ግንዛቤያቸውን ለመፈተሽ ታስቦ 17 ክፍት ጥቄዎች ከሁለቱ ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡት የ2013 ዓ.ም የ7ኛ ክፍል መረጃ ሰጪ መምህራን የቀረበ ነው፡፡ ምንም እንኳን ለቃለ መጠይቅ ብዛት ያላቸው ጥያቄዎች ለመረጃ ሰጪዎች ማቅረብ አድካሚ እና ለትንታኔም አዳጋች ቢሆንም በሁለቱ ዘዴዎች የተገኙ ዘዴዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እና የተሻለ መረጃ ለማግኘት ከሚል በአጥኚዋ በጥናቱ በተካተቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ላሉ ሶስት መምህራን ጋር ቃለ መጠይቅ በማካሄድ መልሶቻቸውን በማስታወሻ ተመዝግቦ ተተንትኗል፡፡ ቃለ መጠይቁ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የመምህራኑን ዳራ ሲይዝ ሁለተኛው የመጠይቁ ክፍል ለጥናቱ የቀረቡ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህምለመረጃ ሰጪ መምህራን የቀረቡ የመረጃ መሰብሰቢያ ጥያቄዎች ለናሙና የተመረጡ መምህራኖች የተሰጡትን መልሶች ለትንተናው ያመች ዘንድ አሉታዊ እና አወንታዊ መልሶች ማለትም አዎን ወይም አይደለም በማለት ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡የተሰጡትን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሾች በሰንጠረዥ ውስጥ ለማስፈር ሙሉ የመላሾች ሀሳብ ከሰንጠረዥ ቀጥሎ ለትንተና በሚያመች መልኩ ተቀምጧል፡፡

### 3.3.4. ፈተና

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ሀዴ በኢ- አፈ ፈት ተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶችን ምንነት እና መንስኤዎችን ለማወቅ ያስችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በፈትና የሚገኘው መረጃ የጥናቱን የመጀመሪያ ጥያቁ ይመልሳል ተብሎ ይገመታል፡፡ በመሆኑም ፈተናውን ተግባራዊ ለማድረግ የተማሪዎቹ ዳራ እና የቋንቋ ችሎታ ያገናዘቡ አስራ አንድ ርዕሶች ከተዘጋጁ በኋላ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ማስተካከያ ተሰቶባቸዋል፡፡

በመቀጠልም እነዚህ ርዕሶች በእጣ ንሞና ለተመረጡ ተማሪዎች ቀርቦ ስለርዕሶቹ በግልጽነት ውይይት ተደርጓል ከይይቱ በኋላም ከተጠቀሱት ርእሶች ተማሪዎቹ ለንግግር የሚመቻቸውን አዳዲስት ርእሶች እንደየ ፍላጎታቸው እና እንደየምርጫቸው ርዕሶቹን ከተከፋፈሉ ቡኋላ ለሁለታ ሳምንት ያህል ተዘጋጅተውባቸው እንዲመጡ ተደርጓል፡፡

የተማሪዎቹን ውጤት አሰጣት በተመለከተ አጥኝዋ ተማሪዎቹ ንግግር ሲያደርጉ በመቅረጸ ድምጽ በመቅዳት በሁለት ፈታኝ መምህራን እንዲሰያቸው ተደርጓል፡፡ የፈተናው ውጤት ከመሰጠቱ በፊት ዘጥኝዋ ለሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለፈተናው ይዘታ ማለትም ፡- ሳልስ አና ሳድስ ፊደላትን ለይቶ መናገር መቻል ፣ የሀሳብ ቀደም ተከተ ጠብቀው መናገራቸውን ፣ ቃላትን በተገቢው ቦታ የመጠቀም ችሎታ /ብቃት/ ያላቸው መሆኑን ፣ ነጠላና ብዙ ቁጥርን ከማሰሪያ አንጽ ጋር አጣጥመው መናገራቸውንና የመደብና የፆታ አጠቃቀም በሚሉት የንግግር ንኡሳን ክሂሎች ላይ በምምስረት ውጤት እንዲሰጡ ተደርጓል ይህም ለእያንዳዱ ንኡስ ክሂል ምን ያህል ነጥብ መስጠት እንዳለባቸው ከመምህራን ጋር በቅድሚያ ውይይት በማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ውይይት ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት በሁለቱ ፈታኞች መካከል የውጤት አሰጣጥ ልዩነት ዝንዳይኖር ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታስቦ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ከላይ ለተጠቀሱት የንግግር ንዑሳን ክሂሎች ለየአንድ አዳቸው ከ20% ውጤት እንዲሰጡ ስምምነት ላይ ተደሷል፡፡ አጥኝዋም በሁለቱ መምህራን የተገኘው ውጤት ለመተንትን፣ ንግግር ያደረጉትን ተማሪዎች ብቻ የመቅረጸ-ድምጽ ንግግር ለትንታኔ ያመች ዘንድ ወደ ጽሁፍ በመቀየር በአባሪ ላይ አስቀምጣለች፡፡

በመጨረሻም ከላይ በቀረቡት ክሂሎች ላይ የተሰጠውን ፈተና እና የመምህራኑን ውጤት መሰረት በማድረግ በአማካኝ ውጤታቸው ላይ በመመስረት በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት በመጠቀም አጥኝዋ ትንታኔ አድርጋበታለች፡፡

## 3.4.የጥናቱ ስነ- ምግባራዊነት

የጥናቱን አላማ ለማስከት የሚያስፈልገው መረጃ ከተለያዩ ወገኖች በተለያዩ ዘዴዎች በሚከተለው ቅደም ተከተል ለማግኘት ተሞክሯል፡፡

ለፈተና ለክፍሉ ውስጥ ምልከታ ፣ ለቡድን ተኮር ውይይት እና ለቃለ መጠይ የሚረዱ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል ፤ በጥናቱ ተተኳሪ የሚሆኑት ታመሪዎች እና መረጃ ሰጪ መምህራንን ፍቃደኝነት በማግኘት በጥናቱ ተካተዋል ፤ የጥናቱን አላማና አስፈላጊነት ለጥናቱ ተሳታፊዎች መምህራንና ተማሪዎች ገለጻ ተደርጓል ፤ የትምህርት በቱን መማር መስተማር ሂደት ባገናዘበ እና ለተሳታፊዎች ያለውን አመቺነት ከግምት ውስጥ በማስገባት መረጃ የሚሰበሰብበት የግዜ ሰሌዳ ተነድፏል ፤ የመረጃ አሰባሰቡ ሂደትም በስረአት ተከናውኗል ፤ ለተማሪዎች የቀረበው ፈተና እና የቡድን ውይይት በመቅረጸ ድምጽ ተቀድቶ ለትንተና እንዲያመች ወደ ጽሁፍ እነዲሸጋገር ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከተማሪዎች እና ከመምህራን የተገኑት መረጃዎች በየአይነታቸው ተተንትነዋል፡፡

## 3.5.የትናቱ አስተማማኝነት

ይህ ጥናት ዋናው ጥናት ከመካሄዱ አስቀድሞ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹን በታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም የሙከራ ጥናት (Pilot Study) ፈተና እና የቡድን ውይይት ጥያቄዎች በመጀመሪያ ፈረቃ ከሦስት ሴክሺን ውስጥ አስር አስር በድምሩ 30 ኢ- አፈ ፈት ተማሪዎች ላይ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገው ግልጽነት የሌላቸው ወይም አሻሚነት ያላቸው ጥያቄዎችን በትናቱ ወቅት የመጠቀም አጋጣሚን ለማስወገድ ስለሚረዳ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የረጅም ግዜ የማስተማር ልምድ ካላቸው የቋንቋ መምራን ጋር በተለይም በጥናቱ ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ የራሳቸውን አስተያየጥ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በመቀጠል የተሰጠውን የማስተካከያ አስተያየት መነሻ በማድረግ እንደገና የማስተካከል እና የመጣራት ስራ ማካሄድ ተችሏል፡፡ በመቀጠልም ለጥናቱ አማካሪ ቀርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማተከከያ ተደርጎ በስራ ላይ ውሏል፡፡

## 3.6. የመረጃ አደረጃጀት እና አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት አላማ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ኪሂል ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ስነ-ዘዴዎች እና ትምህርቱን እንዴት እንደሚተገብሩ ለመፈተሽ የጥናቱን ዝርዝር እና ዋና አላማዎች መሰረት በማድረግ ሲሆን ፤ መረጃን በአጋዝነት ለመሰብሰብ ከተመረጡት ሁለት ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ከተመረጡት ተማሪዎች ከጽሁፍ መጠይቅ ከክፍል ውስጥ

ምልከታእና የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ መምህራ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመልክ በመልኩ ተደራጅተው ከተመደቡ በኋላ ተተንትነዋል፡፡

ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እና ከክፍል ውስጥ ትምህርት አተገባበር ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ውጤት ለየብቻቸው በመለየት በትረካዊ ወይም ገለፃዊ መንገድ ሲቀርቡ፤ ለተማሪዎች የቀረቡትን የጽሁፍ መጠይቆች ለእያንዳንዱ የምርጫ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ተደምሮና በመቶ ተባዝቶ ለቀላል መላሾ ብዛት ተካፍሎ በመቶኛ ተቀምጧል፡፡ ከዚህም የተገኘው አሀዛዊ ውጤት ምን ማለት እንደሆነ ተተንትኗል፡፡ ለክፍት ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾችም ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በመሆኑም ምርምሩን ለማካሄድ ሁለቱንም የምርምር ዘዴዎች ማለት አይነታዊ እና መጠናዊ ዘዴዎችተግባር ላይ በመዋሉ ድብልቅ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በአቀራረቡም ገላጭ የምርምር ስልት ተተግብሯል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# 4. የመረጃ ትንተና ውጤት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲማሩ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች መፈተሽ  የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ መመርመር ነው፡፡

ጥናቱ የሚከተሉትን አላመዎች ይዟል፡፡ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ በአብዛኛው የሚፈፅሙትን ስህተት መለየት፣ ኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲየደርጉ የሚፈፅሙት የስህተት ምንጭ ለይቶ ማሳየት እና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በንግግር ሂደት ላይ የሚታዩ ስህተት እና  የስህተት ምንጮችን የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት ከፈተና የሚገኘው መረጃ እና የክፍል ውስጥ ምልከታው የጥናቱን አንደኛ ጥያቄ ለመመለስ የሚያገለግሉ ፣ የቡድን ተኮር ውይይት ደግሞ አንደኛውንና ሁለተኛውን የጥናቱን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዳ ሲሆን ከቃለ መጠይቅ የሚገኙ መረጃዎች በተራ ቁጥር አንድ ፣ ሁለት አና ሦስት ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ለመመስ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

## 4.1 የመረጃ  ትንተና

### 4.1.1. አፋቸውን በኦሮሚኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?

የሚለውን ይህንን የጥናቱን የመጀመሪያ ጥያቄ ለመመለስ በፈተና እና በክፍል ውጥ ምልከታ አማካኝነት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የተማሪዎቹን የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ችሎታ እና ያለባቸውን ችግር ለመረዳት ለተጠኚ ተማሪዎች ፈተና ተሰጥቷል፡፡ ይህም ሳልስ እና ሳድስ ፊደላትን ለይቶ መናገር መቻላቸውን ፣ የሀሳብ ቅደም ተከተል ጠብቀው መናገራችውን ፣ ተገቢ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ ያላቸው መሆኑን ፣ ነጠላ እና ብዙ ቁጥርን ከማሰሪያ አንቀጽ ጋር አጣጥመው መናገራቸውን እና  የመደብ እና የፆታ ትክክለና አጠቃቀም በሚሉት የንግግር ንዑሳን ኪህሎች ዙሪያ ላይ በመመስረት በፈታኝ አንድ እና በፈታኝ ሁለት መምህራን ከተጠቀሱት ንኡሳን

ኪህሎች ጎልቶ የሚታየው የትኛው እንደሆነ በመለየት እና የችግሩን ጥልቀት ለመግለጽ እንዲያመች በተሰጠው አማካኝ ውጤት ላይ በመመርኮዝ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ አንድ፡-** በሁለት አራሚዎች የተሰጠ ፈተና አማካኝ ውጤት ትንተና

| የተፈታኝ መለያ ዉጥር | ባልሰና ባድስ ፊደላትን ለይቶ መናገር መቻል 20% | | |
|---|---|---|---|
| | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አማከኝ ውጤት |
| 1 | 3 | 3 | 3 |
| 2 | - | - | - |
| 3 | 3 | 4 | 3.5 |
| 4 | 2 | 5 | 3.5 |
| 5 | 4 | 7 | 5.5 |
| 6 | 3 | 5 | 4 |
| 7 | - | - | - |
| 8 | 3 | 5 | 4 |
| 9 | 5 | 3 | 4 |
| 10 | 4 | 3 | 3.5 |
| 11 | 4 | 3 | 3.5 |
| 12 | - | - | - |
| 13 | 4 | 5 | 4.5 |
| 14 | 5 | 3 | 4 |
| 15 | - | - | - |
| 16 | 2 | 5 | 3.5 |
| 17 | 5 | 5 | 5 |
| 18 | 5 | - | 2.5 |
| 19 | 3 | 4 | 3.5 |
| 20 | 4 | 3 | 3.5 |
| 21 | - | - | - |
| 22 | - | - | - |
| 23 | 3 | 4 | 3.5 |
| 24 | 4 | 4 | 4 |
| 25 | 5 | 3 | 4 |
| 26 | 5 | 5 | 5 |
| 27 | 5 | 5 | 5 |
| 28 | - | - | - |
| 29 | 6 | 6 | 6 |
| 30 | 4 | 3 | 3.5 |
| 31 | - | - | - |
| 32 | 4 | 4 | 4 |
| 33 | - | - | - |
| 34 | 3 | 3 | 3 |
| 35 | - | - | - |
| 36 | 4 | 4 | 4 |
| 37 | 3 | 3 | 3 |
| 38 | 3 | 3 | 3 |
| 39 | 5 | 3 | 4 |
| 40 | 6 | 5 | 5.5 |
| 41 | 3 | 6 | 4.5 |
| 42 | 2 | 3 | 2.5 |
| 43 | 4 | 4 | 4 |
| 44 | 3 | 2 | 2.5 |
| 45 | 1 | 3 | 2 |
| 46 | 2 | 3 | 2.5 |
| 47 | 2 | 5 | 3.5 |
| 48 | 3 | 4 | 3.5 |

በአራሚ 1 እና በአራሚ 2 መምህራን አማካኝነት ለተተኳሪ ለማሪዎች በተሰጠ የፈተና ውጤት መረት በማድረግ በአማካኝ ውጤትታቸው ላይ ከዚህ ቀጥሎ የመረጃ ትንተና ተካሂዶበታል፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 1 ለመረዳት የሚቻለው ለፈተና የቀረቡት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ብዛት 48 ሲሆን ፣ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን ለይተው (ጠብቀው) የመናገር ችሎታቸውን በሚለው የንግግር ንኡስ ኪሂል በሁለቱ አራሚዎች የተገኘው አማካኝ ውጤት 2.98 ፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ ሳልስ እና ሳድስ ፊደላትን ለይተው መናገር አለመቻላቸውን ከሁለቱ አራሚ መምህራን አማካኝ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ የተማሪዎቹን በአማሪኛ ቋንቋ የመናገር ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ የቻላል፡፡

| የተፈታኝ አማካኝ ውጤት | የሀሳብ ቅድመ ተከተልን ጠብቆ መናገር 20% | | |
|---|---|---|---|
| | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አማካኝ ውጤት |
| 1 | 3 | 4 | 3.5 |
